የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ– ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 22
ADDIS ABABA - 15th December, 1998


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፻፵፪/፲፱፻፺፩ ዓ·ም
ለሁለተኛው የኢነርጂ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከኖርዲክ ዲቨሎፕመንት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፱፻፳፭


## CONTENTS


Proclamation No. 142/1998
Nordic Development Fund Credit Agreement for Partly Financing the Second Energy Project Ratification Proclamation ........................ Page 925


## አዋጅ ቁጥር ፻፵፪/፲፱፻፺፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ ዲቨሎፕመንት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛው የኢነርጂ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር ፬ ሚሊዮን (አራት ሚሊዮን ኤስ·ዲ·አር·) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ ዲቨሎፕመንት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ሜይ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው የኢነርጂ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከኖርዲክ ዲቨሎፕመንት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻፵፪/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 142/1998

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE NORDIC DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Credit Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Nordic Development Fund stipulating that the Nordic Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 4,000,000 (four million Special Drawing Rights) for partly financing the Second Energy Project, was signed in Abidjan, On the 27th day of May, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 15th day of December, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Nordic Development Fund Credit Agreement for Partly Financing the Second Energy Project Ratification proclamation No. 142/1998."


ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኖርዲክ ዲቨሎፕመንት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ሜይ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ፩፻፺፰ የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘው ኤስ·ዲ·አር ፬ ሚሊዮን (አራት ሚሊዮን ኤስ·ዲ·አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement No. 198 signed in Abidjan on the 27th day of May, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Nordic Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 4,000,000 (four million Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force on the 15th day of December, 1998.

Done at Addis Ababa, this 15th day of December, 1998.

NEGASO GIDADA (DR)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE